# ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

## ከጋሻ ለኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ

ሰሞኑን በመድረክና ሌሎች ተቃዋሚ ሀይሎች አማካኝነት በመላው ኢትዮጵያ በተለይም የህወሓት መሰረት እየተባለ ሲጠራ በቆየው ትግራይ የሚታየው አበራታች ክስተት የአንድነት ስራ እንቅስቃሴ ውጤት ለመሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ይህ የሚታየው ተስፋ የተገኘው የረጅም ጊዜ የጭቆና ውጤት ነውና የተከፈለውም መስዋእትነት ግን ቀላል አለመኖሩ ሁላችንም የተከታተልነው ጉዳይ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ከምርጫ 97 በኃላ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ብቅ ብለው በነበሩበት ወቅት በደምስ በለጠ አዘጋጅነት አቦጊዳ ተብሎ ይጠራ በነበረው የረዲዮ ፕሮግራም ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። በዚሁ ፕሮግራም ከአድማጭ የሚከተልው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። በውጭ ከሚገኙት የትግራይ ተወላጅ ወንድሞቻችን መቃቃር አለ፡ አገር ቤት ውስጥስ ሁኔታው እንዴት ነው? ሲመልሱም "አዲስ አበባ የሚገኘው የመረጠው ቅንጅትን ነው። "በትግራይ የሚኖረው ግን ነፃ እንዳወጣን ሁሉ ነፃ የምናወጣው እኛ ነን።" "ሆኖም እነሱም መታገል አለባቸው" ባሉበት ወቅት ስለ ጭቆናው ብዛት ሲያብራሩ ምሳሌ ሰጥተው ነበር። አንዴ በመቀሌ የኢድዩ አባል ባሉት ሰው ከብዙ ግርፋት በኃላ በከተማው እያዞሩት ነበር ያዋሉት። በዚሁም ሌላው ፈርቶ አርፎ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ ነው።ብሎም ምንም አይነት እንቅሳሴ እንዳያሳይ ነው፡ ብላል።" የኢሰመጉን ቅርንጫፍ ለመክፈት በሞኮሩበትም የህወሓት ካድሬዎች እንደረበሸዋቸው ነበር ያስታወቁት።ከአምስት አመታት በፊት ይህ አይነት መልክ ይታይ በነበረበት ትግራይ ነው እንግዲህ አሁን እድሜ ላአንድነት ሃይሎች ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ የሚታየው። ለአራት አሰርት አመታት የተገነዘብነው ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ አብረው ለሚመጡ የአንድነት ሃይሎች የሚሰጠው ድጋፍ ቅጽበታዊና ፈጣን ነው።

ወታድሩና ሌላው የህብረተ-ሰቡ ክፍል አንድ ሆኖ በተነሳበት ወቅት ንጉሱን ለማውረድ ከባድ አለመኖሩ የሚታወስ ነው። በቀላሉ የተገኘ ለውጥ ስለነበረ ነው መሰል ያስከተለው መዘዝ ግን እስከ አሁንም ቢሆን ሊያባራ አልቻለም።ደርግም ቢሆን አጀማመሩ ላይ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ የነበረው መሆኑን አሌ የሚባል ሃቅ አይሆንም። ኢህአፓና ሌሎች የአንድነት ሃይሎችም ቢሆኑ እንደዚሁ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ የተቸራቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ ባደረጉት እንቅስቃሴ ለመኖሩ በታሪክ መዛግብት የሰፈረ ነው፡፡ ከአምስት አመታት በፊት ቅንጅትና ህብረት የነበራቸው የህዝብ ድጋፍም ሲታይ እንደዚሁ ባጭር ጊዜ ውስጥ በተደረገው እንቅሰቃሴ ለመኖሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ይሁን እንጂ የአንድነት ሃይሎች በተለይም ኣመራሩ በፀና መንፈስና ብልህነት በተሞላበት ኣንድነቱን ኣስጠብቆ ዘለግ ላለ ጊዜ ሳይጉኣዝ በመቅረቱ የኢትዮጵያ ህዝብ እስከኣሁንም ቢሆን ነጻነቱን ሊቀዳጅ ኣልቻለም። እንዲያውም ለኣንድነት ሃይሎች በሚያሳየው ድጋፍ የደረሰው ተደጋጋሚ ዘግናኝ ጥቃት ስናስታውስና ኣሁንም ቢሆን ግን ለለውጥ ያለው ፍላጎት ሳይገታ በትግሉ መቀጠሉ በጣም የሚደነቅ ነው።

የወቅቱ ያኣንድነት ሃይሎች ተኪ ወይም ወራሽ ሆኖ ብቅ ያለው መድረክም በህዝቡ የሚሰጠው ድጋፍ እንደ ቀደምቱ ያኣንድነት ድርጅቶች ከፍተኛ ነው።ይህ ሁሉ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት ምን ያህል እንደጉኣጉኣ ነው።በተለይም የብርቱኩኣንን ኣይነት ፅኑና መንፈሰ ጠንካራ መሪ በሚያገኝበት ጊዜ ህይወቱን ለመስጠት ወደኁኣላ የማይል ለመሆኑ በተደጋጋሚ ኣሳይታል። ቃልዋን ሳታጥፍ ለእወነት በፅናት በመቆሙዋም እንደስዋ ብዙ መንፈሰ ጠንካራና ጀግኖች ብቅ ብቅ እያሉ ነው።በኣድዋ የነበለቱ ተወላጅ ኣቶ ኣረጋዊ ገ/ዮሃንስ ኣንዱ ናቸው።በድብደባ ብዛት በሞት ኣፋፍ ሆኖው በቪኦኤ ድምፃቸው ያሰሙት በኣክሱም ኣውራጃ የውቅሮው ሰውና በኣሩሲ ክፍለ ኀገር የኣርባ ጉጉ ኣውራጃ ለፌዴራል ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ የቅርብ ጊዜ የፅኑ ዜጎች ተምሳሌት ናቸው።

የኢያሌ ጀግኞች ኢትዮጵያዉያን ስቃይና የፈሰሰው ደማቸው ግን የነፃነቱን ድል እያቃረበው ለመሆኑ የሚያጠራጥር ኣይሆንም። ከኢትዮጵያውያን ኣልፎ የኣለም ህብረተሰብ ሁሉ የህዝባችንን ግፍ ምን ያህል የከፋ ለመሆኑ በዝርዝር እያስተጋቡት ይገኛሉ። የሃገር ቤቱን የነጻ ሚዲያዎች መዝጋቱ ኣልበቃ ብሎ ቪኦኤ እንዳይደመጥ የኢትዮጵያ መንግስት ባፈነበት ማግስት ለሰው ልጆች ክብርና በሰላም መኖር የቆሙ Human Right Watch እና Amnesty International ኣለም ኣቀፍ ተቁኣማት ድምፃቸውን ከፍ ኣድርገው እያሰሙ ነው።በመሆኑም የኣመሪካውም ምክር ቤት በኢትዮጰያ ጉዳይ ውይይት ጀምሯል። የመለስ መንግስት ኣምባገነን መሆኑና ምርጫ ምርጫ የሚለውም ለመደለያና የግፍ ኣገዛዙን ለመቀጠል በመሳሪያነት የሚጠቀምበትን የጸጥታ ሃይሉን መመገብ የሚያስችለውን እርዳታ እንዳይቁኣረጥበት ለማድረግ መሆኑን በትክክል ተገንዝበውታል። ስለሆነም መስዋእት የሆኑት ጀግኖቻችን ለተቀረው ውጤት እያስገኙለት ነው።የእውነት ክር ትመነምናለች እንጂ ኣትበጠስም ይባል የለ።Force Never disproves Truth! በሚል ርእስ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ከምርጫው በኋላ መጻፋቸውም ኣይዘነጋም።ያለፈውን ውሸት ለመሸፈን በሌላ ውሸት እየሞጎቱ ምን ያህል ይዘለቅ ይሆን? ግማሽ መንገድ ኣልፈን ተቃዋሚዎችን እናስተናግዳቸዋለን፣እንቀበላቸዋለን፣ ጠንካራ ተቃዋሚ እኮ የኣይንህን ጉድፍ መሳይ የምታይበት መስተዋት ነው እየተባለ የተፌዘት ጊዜ ሩቅ ኣይደለም። ይሁን እንጂ ከግማሽ መንገድም ታልፎ ለሃገሪቱ የሚበጁ በህዝብ ፊት ሲነገር ሊዋጥላቸው ኣልቻለም። ከሃቅ ጋር ከተራራቁ ብዙ ጊዜ በማለፉ ኣሁን ድንገት ደርሰው ደግ ሰዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ በቀላሉ የምንረዳው ጉዳይ ነው። ይልቁንስ ያልሆኑትን ነን እያሉ የማያደርጉትን ኣደርጋልሁ እያሉ አሉባልታ በማስፋፋት ለብዙ ዜጎቻችን የህይወት ጠንቅ ለመፍጠር ሽርጉድ ማልቱ ማቆም ይኖሩባቸዋል ።በተጨማሪም በኣቶ ኣረጋዊ ገ/ዮሃንስ የተፈጸመው ኣሰቃቂ ግድያና በሌሎች ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በየቀኑ በመደረግ ላይ ያለዉ ኣረመንያዊ ድብደባዎች እስራቶችና ግድያዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማቆም አለባቸዉ እንላለን።

ግራም ነፈሰ ቀኝ ያለንበት ወቅት ባኣንጻራዊ መልኩ ሲታይ ለፍትህ ለቆሙት የኣንድነት ሃይሎች እያጋደለ በመምጣት ላይ በመሆኑ ሁኔታው የበለጠ ለወገንና የዲሞክራሲ ሃይሎች እየተመቻቸ እንዲሄድ ኣንድነታችንን ከምን ጊዜም ኣጠናክረን ወደፊት እንድንገፋ ጋሻ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ድል ለፍትህና ዲሞክራሲ ለቆሙት ያኣንድነት ሃይሎች!

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን

ሲያትል ዋሽንግተን

ኤፕሪል 03 2010 በፈረንጆች